በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ.209757

ቀን፡-30/03/2014ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካቾች ፡1ኛ/ አቶ ከበደ ደሴ } ጠበቃ ይልማ አቻሜ

2ኛ/ አቶ ደግፍ ባረዳ

ተጠሪዎች ፡1ኛ/ ወ/ሮ እልፍነሽ አብደላ } ጠበቃ ሰለሞን ታደሰ ቀረቡ

2ኛ/ ወ/ሪት ትዝታ ፈቀደ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የሽያጭ ውል የሚመለከት ነዉ፡፡ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪዎች ከሳሽ በመሆን በአመልካቾች ላይ በሁለት የተለያዩ መዝገቦች ላይ ባቀረቡት ክስ አመልካቾች በደራጀማ ሆቴል ኃ/የተ/የግ/ማህበር ውስጥ ስድስት አክሲዮኖችን ከአንድ ሱቅ ጋር እንሸጥላችኋለን በማለት በ2004 ዓ.ም በተደረገው ውል ለ1ኛ ተጠሪ በብር 450,000.00 እንዲሁም ለ2ኛ ተጠሪ በብር 480,000.00 የሸጡልን ቢሆንም ውሉ ከህግ ውጪ የተደረገ በመሆኑ አመልካቾች በሽያጭ ውሉ መሰረት የወሰዱት ገንዘብ እንዲመልሱልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡አመልካቾች በበኩላቸዉ ውሉ የተደረገው በቃል መሆኑንና አንደኛው ተዋዋይ በውሉ ጥቅም አለማግኘቱ የውል ማፍረሻ ምክንያት አይሆንም፣የተሸጠው በሱቅ የመጠቀም መብት እንጂ የሱቅ ባለሀብት እንዲሁም የአክሲዮን ድርሻ ላይ አይደለም፣ተጠሪዎች ሱቁን በመረከብ ሲጠቀሙበት ቆይቷል፤ይህም በሱቁ ላይ ጥቅም ሲያገኙ እንደነበር የሚያሳይ ነው፣ተጠሪዎች የከፈሉት ገንዘብ የሚመለስበት የህግ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አግባብ የለም፣ማህበሩ የሚሰራበት ቤት ከቤቶች ኮርፖሬሽን በመከራየት ነዉ፤በመሆኑም ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ክርክር እና የቀረበውን ማስረጃ መርምሮ ደራጀማ ሆቴል ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሚሰራበት ቤት ንብረትነቱ የመንግስት ሆኖ አመልካቾች የመጠቀም መብታችን ነው የሸጥንላቸው የሚሏቸው ሱቆች በምን አግባብ አግኝተው የመጠቀም መብታቸውን እንደሸጡ አላስረዱም፤አመልካቾች ለክርክሩ ምክንያት የሆኑ ሱቆች ላይ ምንም አይነት በህግ የተረጋገጠ መብት ሳይኖራቸው ሱቆቹ የእኛ ናቸው በማለት ለተጠሪዎች የሸጡላቸው መሆኑ ስለተረጋገጠ የሽያጭ ውሉ ፈርሶ ግራ ቀኙ ወደ ነበሩበት ሊመለሱ ይገባል በማለት የሽያጭ ገንዘቡን ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ከ9% ወለድ ጋር ለተጠሪዎች እንዲመለሱላቸው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበዉ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ክርክር ከሰማ በኋላ መዝገቡን መርምሮ ውሉ ፈርሶ ገንዘቡ ለተጠሪዎች እንዲመለስ የተባለዉን በማጽናት ወለዱ መታሰብ ያለበት ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን እንደሆን በማለት አሻሽሎ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ላይ ነዉ፡፡ውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፤1ኛ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ጉዳዩን በሽማግልና በዕርቅ ጨርሰን የእርቅ ስምምነቱን ለፍ/ቤቱ አቅርበን ክርክሩ እንዲቋረጥ አመልክተን ፍ/ቤቱም መጋቢት 1 ቀን 2013ዓ.ም በዋለው ችሎት ክርክሩ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 278(1) መሰረት ተቋርጧል ብሎ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ ሚያዝያ 18 ቀን 2013 ዓ.ም ውሳኔ ሲሰጥ ብር 450,000.00 ለ1ኛ ተጠሪ ይክፈል በማለት የሰጠው ውሳኔ ስህተት ነው፤የስር ፍ/ቤት ሁለቱም አመልካቾች ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ብር 480,000.00 ለ2ኛ ተጠሪ እንዲከፍሉ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን ከፍተኛ ፍ/ቤት ግን 2ኛ አመልካች ብቻውን እንዲከፍል በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት ውሉ ፈርሶ ተዋዋዮቹ ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ በማለት ገንዘቡ ለተጠሪዎች እንዲመለስ ሲወስን ሱቆቹ ደግሞ ለአመልካቾች እንዲመለስ መወሰን ሲገባ ይህንን በዝምታ ማለፉ ስህተት በመሆኑ ውሳኔው እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካቾች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ፍ/ቤቱ በ1ኛ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ መካከል የነበረው ክርክር በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 278(1) መሰረት ተቋርጧል በማለት ክርክሩ በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል እንዲቀጥል ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ 1ኛ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ብር450,000.00 እንዲከፈል እንዲሁም 2ኛ አመልካች ለ2ኛ ተጠሪ ብር 480,000.00 እንዲከፍሉ የወሰነበት አግባብ ለማጣራት ጉዳዩ ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ ታዟል፡፡

ተጠሪዎች ባቀረቡት መልስ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የእርቅ ስምምነቱን መዝግቦ እያለ 1ኛ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ብር 450,000.00 እንዲከፍሉ የሰጠው ውሳኔ ባለማስተዋል የተፈፀመ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል፤ክርክሩ ሊቀጥል አይገባም፡፡የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ብር 480,000.00 እስከነወለዱ አመልካቾች ለ2ኛ ተጠሪ ባልተነጣጠለ ኃላፊነት የሰጠዉን ውሳኔ

ከፍተኛ ፍ/ቤት ያፀና ቢሆንም በውሳኔው ላይ 2ኛ አመልካች ብቻ ፍርድ ያረፈበት ገንዘብ ለ2ኛ ተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ ስህተት በመሆኑ ሊታረም እንደሚገባ እናምናለን ነገር ግን መሰረታዊ የህግ ስህተት አይደለም፤ሱቆቹ በተጠሪዎች እጅ የሌሉ እና ንብረትነቱ የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ስለሆነ ለአመልካቾች ሊናስረክብ አንችልም፤በዚህ ረገድ የቀረበው ቅሬታ ውድቅ እንዲሆን በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካቾች አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አንጻር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ በአመልካቾች እና ተጠሪዎች መካከል የተደረገዉ የሽያጭ ዉል እንዲፈርስ የተወሰነዉ አመልካቾች ሊተላለፍ የሚችል መብት ያላቸዉ ስለመሆኑ ኣላስረዱም ተብሎ ነዉ፡፡በዚህ ረገድ የቀረበ ቅሬታ የለም፡፡ይህንኑ ተከትሎ አመልካቾች በዉሉ መነሻ የተረከቡትን ገንዘብ ለተጠሪዎች እንዲመልሱ የተወሰነ ሲሆን የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነዉ የገንዘቡን አመላለስ በተመለከተ ይግባኝ ሰሚዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፈጸመዉ ስህተት እንዲታረም በማለት ነዉ፡፡ተጠሪዎችም ቢሆኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ስህተት እንዳለበት አምነዉ ነገር ግን በዚያዉ ፍርድ ቤት ሊታረም ይችላል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡እኛም በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ዉሳኔ አግባብነት በቅደም ተከተል መርመረናል፡፡

የመጀመሪያዉ በ1ኛ አመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገዉ ዉል የሚመለከት ነዉ፡፡ከክርክሩ እንደተገነዘበነዉ በሁለቱ መካከል የተደረገዉ ዉል መፍረሱንና ዉጤቱን በሚመለከት በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ላይ አመልካች ቅር ተሰኝተዉ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በክርክር ሂደት ላይ እያሉ ጉዳዩን በስምምነት በሽምግልና መጨረሳቸዉን ገልጸዉ ማመልከቻ በማቅረባቸዉ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤትም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 278/1/ መሰረት ክርክሩ እንዲቋረጥ በቀን 01/07/2013ዓ.ም ትእዛዝ ስለመስጠቱ መዝገቡ ያሚያል፡፡ግራ ቀኙም አልተካካዱም፡፡በፍትሓብሔር ስነስርዓት ህጉ እንደተመለከተዉ በፍርድ ቤት በክርክር ላይ ያሉ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸዉን ከፍርድ ቤት ዉጪ በስምምነት ለመጨረስ የተስማሙ ከሆነ እና ይህንኑ ለፍርድ ቤቱ ሲያቀርቡ ፍርድ ቤቱ የእርቅ ስምምነቱ ለሞራል እና ለህግ ተቃራኒ አለመሆኑን ካረጋገጠ በኋላ እርቁን ተቀብሎ በማጽደቅ መዝገቡን እንደሚዘጋ በሌላ በኩል ደግሞ ተከራካሪ ወገን ክሱን ወይም ክርክሩን ለማቋረጥ ሲፈልግ ይህንኑ ለፍርድ ቤቱ ካሳወቀ ክርክሩ እንዲቋረጥ ትእዛዝ የሚሰጥበት ሁኔታ ተመልክቷል፡፡(የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 277 እና 278 ድንጋጌዎችን ይመለከታል)፡፡ በሁለቱ ድንጋጌዎች መካከል የምክንያት እና የዉጤት ልዩነት መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ እንዲህ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቱ በስረነገሩ ወይም አከራካሪዉ ጉዳይ ላይ ፍርድ እንዲሰጥ አይጠበቅበትም፡፡ይልቁንም እንደ ተከራካሪ ወገኖች ጥያቄ ስምምነቱ የሚፈጸምበትን አግባብ ወይም ሌላ ተገቢ መስሎ የታየዉን ትእዛዝ መስጠት እንዲችል ስነስርዓት ህጉ ይፈቅድለታል፡፡ፍርድ ቤቱም ይህንኑ ስነስርዓታዊ ጉዳይ ላይ እንዲወሰን ይጠበቃል፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ በ1ኛ አመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል በተደረገዉ ዉል የተቀባበሉትን ብር 450,000 አመላለስ አስመልክቶ ስምምነት ማድረጋቸዉ ስለገለጹ ክርክሩ በፍ/ብ/ስ/ስ ህግ ቁጥር 278/1/ መሰረት እንዲቋረጥ ከተደረገ በኋላ በዚህ ጉዳይ ፍርድ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ቤቱ ዉሳኔ መስጠቱ ስነስርዓታዊ መሰረት የለዉም፡፡ስለዚህም 1ኛ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ብር 450,000 እንዲከፍሉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ በግራቀኙ ጠያቂነት ክርክሩ እንዲቋረጥ የሰጠዉን ትእዛዝ ከግምት ያላስገባ እና የክርክር አመራር ስርዓት ግድፈት የተፈጸመበት ከመሆኑም በተጨማሪ ስምምነታቸዉንም ዋጋ የሚያሳጣ ስለሆነ ሊታረም ይገባል፡፡

ሁለተኛዉ የቅሬታ ነጥብ በሁለተኛ ዉል መሰረት ገንዘቡን የመመለስ ግዴታ የ2ኛ አመልካች ብቻ እንደሆነ ተደርጎ መወሰኑ ተገቢ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነዉ፡፡ከክርክሩ እንደሚታየዉ ሁለተኛዉ ዉል የተደረገዉ በ2ኛ ተጠሪ እና በአመልካቾች መካከል ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተዉ ፍርድ ቤትም በሁለተኛዉ ዉል መሰረት አመልካቾች ከ2ኛ ተጠሪ የተቀበሉትን ብር 480,000 በአንድነትና በነጠላ ለ2ኛ ተጠሪ እንዲመልሱ ወስኗል፡፡ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ይህንን የአንድነትና የነጠላ ሃላፊነት የለወጠበት ምክንያት ስለመኖሩ በዉሳኔዉ ላይ አላተመላከተም፡፡ከመሰረቱም ገንዘቡን የመመለስ ሃላፊነት የአንደኛዉ ወገን ብቻ ነዉ የሚል ክርክር በአመልካቾች በኩል አልቀረበም፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የክርክሩን ይዘት ባለማገናዘብ የተፈጸመ ስህተት ነዉ ከሚባል በስተቀር ሌላ አሳማኝ ምክንያት የለዉም፡፡ስለሆነም በሁለተኛዉ ዉል መሰረት ከ2ኛ ተጠሪ የተቀበሉትን ብር 480,000 አመልካቾች በአንድነትና በነጠላ ለ2ኛ ተጠሪ እንዲመልሱ በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ተገቢ ሆኖ እያለ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት 2ኛ አመልካች ብቻ እንዲከፍሉ መወሰኑ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

የመጨረሻዉ ነጥብ ዉሉ መፍረሱን ተከትሎ ተጠሪዎች ሱቁን እንዲመልሱ ዉሳኔ አለመስጠቱ ስህተት ነዉ የሚል ሲሆን በተጠሪዎች በኩል የቀረበዉ ክርክር ከጅምሩም ቢሆን ሱቅ የተባለዉ የመንግስት ቤት ስለመሆኑና በእጃቸዉ የሌለ መሆኑን በመግለጽ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ስህተት የለዉም በሚል ተከራክረዋል፡፡አንድ ዉል ሲሰረዝ ወይም ሲፈርስ ተዋዋይ ወገኖች በተቻለ መጠን ከዉሉ ከመደረጉ በፊት እንደ ነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ ማድረግ እንደሚገባ የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 1815 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡በተያዘዉ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት የሽያጭ ዉል ሊፈርስ ይገባል በማለት አመልካቾች የወሰዱትን ገንዘብ ለተጠሪዎች እንዲመልሱ ሲወስን የዉሉ ጉዳይ ሱቅ በሚመለከት በግልጽ ያለዉ ነገር የለም፡፡ይሁንና አመልካቾች ለተጠሪዎች ሸጠናል የሚሉት ሱቅ ወይም በሱቁ የመጠቀም መብት ያላቸዉ መሆኑን አላስረዱም የሚለዉ የፍርድ ቤቱ ዉሳኔ ምክንያት የሚያሣየዉ አመልካቾች ሱቅ ለተጠሪዎች አላስረከቡም የሚል ግንዛቤ በመዉሰድ እንደሆነ የሚያሳይ ነዉ፡፡በእርግጥ አመልካቾች ቤቱን (ሱቁን) ለተጠሪዎች አስረክበዉ ከነበረ የርክብክብ ማስረጃዉን በመያዝ እንዲመልሱላቸዉ መጠየቅ የሚከላከላቸዉ ምክንያት ስለመኖሩ በፍርዱ ላይ አልተገለጸም፡፡ከጅምሩም ቢሆን ዉሉ እንዲፈርስ የተደረገዉ አመልካቾች በሽያጭ ለማስተላላፍ ዉል የገቡበት ንብረት ላይ መብት የሌላቸዉ እና ሊፈጸም የማይቻል ዉል መሆኑን በማረጋገጥ ስለሆነ በዚህ ረገድ አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ሲጠቃለል የገንዘቡን አመላለስ በተመለከተ ብቻ ከላይ በዝርዝር በተገለጸዉ ምክንያት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ የስነስርዓት ግድፌት የተፈጸመበት መሆኑን በመገንዘብ እና ይህንኑ በማረም ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

*ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

## ዉሳኔ

1ኛ/የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/247093 ላይ በቀን 18/09/2013ዓ.ም ላይ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ በማሻሻል የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2ኛ/በ1ኛ አመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገዉን ዉል በሚመለከት ብር 450,000 አመላለስ ላይ ከፍርድ ቤት ዉጭ መስማማታቸዉን ገልጸዉ ባቀረቡት አቤቱተ መሰረት ክርክሩ በፍ/ብ/ስ/ስህግ ቁጥር 278/1/ መሰረት እንዲቋረጥ ከተደረገ በኋላ ገንዘቡን እንዲመላለሱ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡

3ኛ/በሁለተኛዉ ዉል መሰረት ከ2ኛ ተጠሪ የተቀበሉትን ብር480,000 አመልካቾች በአንድነትና በነጠላ ለ2ኛ ተጠሪ እንዲለመሱ በሚል ተሻሽሏል፡፡

4ኛ/ወለድን እና ወጪ ኪሳራ የሰጠዉ ዉሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡

4ኛ/በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

3ኛ/በዚህ መዝገብ ላይ በ30/10/2013ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረዉ የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሂ/መ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም